# ቆይታ ከአዳም ረታ ጋር

ገዛኸኝ መኮንን

(ብሌን መጽሔት፣ ቅጽ 8 ቁጥር 2 ዓመተ ምሕረት 2007)

አዳም ረታ የፈጠራ ድርሰት ሥራዎች በብዛት በማይታተሙበት ዘመን በርካታ ሥራዎች በተከታታይ በማሳተም ሥነ-ጽሑፋችንን ያዳበረልን ተወዳጅ ደራሲ ነው፡፡ በቅርቡ ከሚኖርበት አንታሪዮ (ካናዳ) መጥቶ መረቅ የተሠኘ ሥራውን በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ባስመረቀበት ጊዜ ተገናኝተን ያደረግነውን አጭር ጭውውት ለብሌን መጽሔት እንደሚከተለው እቅርቤዋለሁ፡፡

ጭውውቱን ያደረግሁት በግዮን ሆቴል ሳባ አዳራሽ ፊት ለፊት በሚገኘው መናፈሻ ውስጥ ነበር፡፡ ለጭውውት አረፍ ባልንበት ቦታም ጉንዳን ነበረና ጭውውታችን የጀመረው በጉንዳኖቹ ቁንጥጫ ነው፡፡

ገዛኸኝ፡ ጉንዳን አለ፣ አይገርምም?

አዳም፡ አንተ... ወረውሃል

ገዛኸኝ፡ አራግፈው፣ አራግፈው

አዳም፡ ትንሽ የመቆነጠጥ ትዝታን ያመጣል፡፡

ገዛኸኝ፡ እስቲ ስለ ጉንደን እናውራ፡፡ በልቦለዶችህ ውስጥ ጉንዳን አለ እንዴ?

አዳም፡ ጉንዳን... ጉንዳን... እ... ጉንደን አለ፣ አንድ ቦታ ይመስለኛል፡፡

ገዛኸኝ፡ ሣር ላይ ተኝቶ የወረረው ልጅ ነወ..

አዳም፡ አይ፣ የዕውር ጉንዳኖች ሰልፍ የሚል ምናባዊ (imaginary) የመጽሐፍ ርዕስ አለ፣ እቴሜ ሎሚ ሽታ ውስጥ፡፡

ገዛኸኝ፡ ቆይ ጉንዳኑን አራግፍ፣ አዳም ወሮሃል... እንደሱ

አዳም፡ አነቃቃኝ... እና እቴሜቴ ውስጥ እንደ ማጣቀሻ (reference) የተጠቀምኩት እንጂ በብዙ ስለ ጉንዳን የለም፡፡

ገዛኸኝ፡ አሃ...

አዳም፡ ምናልባት መረቅ ውስጥ ማከዳን ወዳጇ ወደ ስምጥ ሸለቆ ለሽርሽር ሲወስዳት ግራር ጋ እንጫወት፣ ምናምን ይላታል... የለም፣ ጉንዳን እፈራለሁ ትላለች፡፡ ሁለት ጊዜ ብቻ ጉንዳን አለ ማለት ነው በሥራዎቼ ውስጥ

ገዛኸኝ፡ እና አሁን ምን ተሰማህ? በስንት ዓመትህ ነከሰህ ጉንዳን?

አዳም፡ ጥሩ አጋጣሚ ሆነ፣ በ30 ዓመት ምናምን ይመስለኛል፡፡

ገዛኸኝ፡ ለመሆኑ የት ነው ተወልደህ ያደግከው? በትክክል ሠፈርህ የት ነበር?

አዳም፡ አዲስ አበበ ነው ተወልጄ ያደግኩት፡፡ ሠፈሬን አሁን አለርት፣ ዘነበ ወርቅ የሚባለው አካባቢ ነው፡፡ ዶሮ ማነቂያ ከምትባል ቦታ ነው፡፡

ገዛኸኝ፡ ከመሐል ከተማዋ ዶሮ ማነቂያ ሌላ...?

አዳም፡ ትንሽ ዶሮ ማነቂያ ነበር... አዎን...

ገዛኸኝ፡ ዶሮ ማነቂያን ሌላ ሥራህ ውስጥ ጠቅሰሃታል፣ እሷ ናት ወይስ የፒያሳዋን?

አዳም፡ እሷን አይደለም፡፡ ይህችኛዋ ዶሮ ማነቂያ ገጠር ናት፣ የፒያሳ ጠባይ የላትም፡፡ እዚያ ነው ያደግኩት፡፡ ከዚያ አሁን ታቦት ማደሪያ የሚባል ቦታ ሄድኩ፡፡ ከስንት ዓመቴ ጀምሮ ነው? ከስምንት ዓመቴ ጀምሮ ከዚያ ነው የነበርኩት፣ ከአገር እስከወጣ ድረስ ማለት ነው፡፡

ገዛኸኝ፡ አንተ ራስህ ከተሜ ነኝ ነው የምትለው ወይስ ከዚህ መረቅ መጽሐፍህ ውስጥ እንደምትለው መዲባ (suburbaner) ነህ?

አዳም፡ አዎ የመዲባ ዜጋ (መዲና እና ባላገር እንደማለት) ነኝ፡፡

ገዛኸኝ፡ ከፊል ከተሜ ከፊል ገጠሬ፡፡

አዳም፡ የእኛ አገር መዲባ በለው፡፡

ገዛኸኝ፡ ግን እኮ እኛ አገር የለየለት ከተሜ አለ ብለህ ታስባለህ?

አዳም፡ ያኔ መሐል ከተማ መጥተን ተምረን ነው የምንመለሰው፤ ስለዚህ ሕይወታችን የተበወዘ ነው፡፡ ግማሽ ከተሜ ትሆናለህ፣ ግማሽ ገጠሬ አትሆንም፡፡ ግን የገጠር ሥራ ነው የምትሠራው እና አዳጋች ነው፡፡ የእኛ አገር መዲባ ናት፡፡

ገዛኸኝ፡ አጋም መብላት፣ ቀጋ መብላት...

አዳም፡ አዎን፣ አሁን እዚያ ታሪክ ውስጥ የምናነባቸው ገለጻዎች ልጅ እያለሁ የኖርኩባቸው ናቸው፣ በጣም ቆንጆ ቦታ ነው፡፡

ገዛኸኝ፡ አሁን ካናዳ ኖረህ ስትመጣና እውነተኛውን የከተሜ ሕይወት ካየህ በኋላ አዲስ አበባን እንደ ከተማ ነው የምታያት?

አዳም፡ የከተሜነት ባህል (urban culture) ድሮም ያለ አይመስለኝም፡፡ እምልህ ልጅ እያለንም አዲስ አበባ ውስጥ ቸርችል ጎዳና ላይ አህያ ጭድ ተሸክሞ ይሄዳል... ተስፋው ነበር እንጂ እርግጠኛው የከተሜነት አኗኗር ባህል አልነበረም፡፡ በቂ ያራዳ ልጅ አልነበረም፡፡

ገዛኸኝ፡ አሁንም ቢሆን ብዙ የተለወጥን አይመስለኝም፤ ብዙ ወደ ኋላ የሚስቡን ትዝታዎች አሉን...

አዳም፡ የገጠርነት አብዮት ከመጣ በኋላ ወደ ገጠርነት ሲለወጥ (de-urbanize ሲያደርግ) ወይም ገጠርን መሠረት ያደረገ ኢኮኖሚ ሲጀምርና በፖለቲካውም በምኑም ከተማው ውስጥ ያለው ሲበተን ከተማ ገጠር (ruralized) ይሆናል፣ ወይም ይገጥራል ማለት ይቻል ይሆን? እና ትንሽ ቆይተህ መከተም (urbanization) ልትጀምር ስትል ሌላ ዓይነት ነገር ይመጣል፡፡ እና አዲስ አበባ ሁሌም እንደ ዳዳች ናት ለመገጠር (ruralized ለመሆን)፡፡ አሁን ምንም እንደማላውቅ ትንሽ ዞሬ መኖር አለብኝ፣ ያንን ለመረዳት ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ጥሩ መረጃ ያስፈልጋል፣ ምን ያህል የከተሜነት ባህል እንዳለ፣ ምን ያህል እንደሄድን... እንጂ ድሮ እንኳን በቂ ከተሜነት ያለ አይመስለኝም፡፡

ገዛኸኝ፡ ወደ ድርሰቶችህና ወደ ሥራህ ልምጣና እንደሚታወቀው አሁን ካናዳ ነው የምትኖረው፡፡ እና ተደጋግሞ ሲባል እንደምንሰማው አንድ ደራሲ ወይም ኬኒ ከቀዬውና ከትውልድ ሥፍራው ከራቀ ከባሕር እንደ ወጣ ዓሣ ነው ይባላል፡፡ አንተ ግን ይህን አባባል ያስተባበልክ (disprove ያደረግክ) ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ብዙዎቹን ሥራዎችህን ከወጣህ በኋላ ነው የሠራሃቸው፡፡ እስቲ ንገረኝ ስለዚህ ጉዳይ፡፡

አዳም፡ ይሄን ከአገሩ ከወጡ በኋላ አይጻፍም የሚል አባባል ማን እንዳመጣው አላውቅም፡፡ ይሄ ዓይነት ነገር እንዴት ሊኖር ይችላል? አባባሉ እንዴት እንደተፈጠረም አላውቅም፡፡ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ደጋግሞ ቀርቦልኛል፡፡

ገዛኸኝ፡ ምናልባት ጥቂት የማይባሉ ደራስያን፣ ለምሳሌ ሰለሞን ደሬሳን ማንሳት እንችላለን እንዲያው በስም እንጥራ ካልን፡፡ ሌሎችም ከወጡ በኋላ አይሠሩም፣ ከአገራችን ልምድ ተነስተን ስናየው፡፡

አዳም፡ የግል ጉዳይ ነው እንጂ መሥራት ይችላሉ... ዘበት እልፊቱን ሠርቷል ሰለሞን ቢቆይም፡፡ ስለዚህ ይቻላል፣ ምክንያቱም ትውስታህን ይዘህ ነው የምትሄደው፣ አካልህንም ይዘህ ነው የምትሄደው፡፡ የምታስታውሳቸው ልምዶች፣ ትዝታዎች አሉ፡፡ አዳጋች የሚሆነው ኃይለኛ እውናዊ (realist) ሆነህ ልቦለድ ልጻፍ ብለህ ከመጣህ ነው፡፡ እስካሁን የምጽፋቸው በአብዛኛው ያለፉ ነገሮች ናቸው፡፡

ገዛኸኝ፡ ሆነ ብለህ፣ ሥራዬ ብለህ ነው ያለፈው ነገር ላይ የተጣበቅከው ወይስ ምርጫ ማጣት ነው የአሁን ጉዳዮች ላይ እንዳታተኩር ያደረገህ?

አዳም፡ በደንብ የማውቃቸው እነዚያን ነው፡፡ መሥራት የሚገቡኝ ነገሮች ያሉ ይመስለኛል፡፡ የመጻፍ ሂደት (process) መፍትሔ (solution) የመፍጠር ብቻ አይደለም፡፡ ያለፈውን ነገር በግልህ ለመረዳት የምታደርገው ጥረት ነው፡፡ እና ለአንባቢህ ስትሰጥ ያንን ለማካፈል የምታደረገው ጥረት ይመስለኛል፡፡ ከ20 ዓመት በፊት ለሆነው ነገር መፍትሔ ልስጥ ብል አይሆንም፣ ምክንያቱም ጊዜው አልፏል፡፡ ግን አንዳንድ ሊለወጡ የማይችሉ ሂደቶችን በድርሰትህ ውስጥ በማንሳት ቢያንስ ያለፈውና የአሁኑ ምን ዓይነት ግንኙነት እንዳላቸው ለማሳየት ትሞክራለህ፡፡

ገዛኸኝ፡ ታሪክ (history) ለአንተ ምንድን ነው?

አዳም፡ ታሪክ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ታሪክ ማለት ያለፈ ጊዜ ማለት ነው፡፡ ዛሬ ዕድሜን ብትጠይቀኝ አምሳ ብልህ ቁጥር ብቻ አይደለም፡፡ እዚያ ውስጥ ሐሳቦቼ አሉ፣ ልምዶቼ አሉ፣ ሳቅ አለ፣ ለቅሶ አለ፤ ብዙ ነገር አለ፡፡ እና ታሪክ የሰው ልጅ አንዱ ማዕከላዊ ክፍል ይመስለኛል፡፡ መዘንጋት የሚቻል አይደለም፡፡ ታሪክ አስፈላጊ አይደለም የሚልህ ስላለፈው ዐሥር ዓመት ጥሩ ትዝታውን አንስቶ ሊያወራህ ይችላል፡፡ እና ያኔውኑ ታሪክን ሲቃወም ልታገኘው ትችላለህ፡፡ ስለዚህ ታሪክ የሚጠየቅ ነገር አይደለም፡፡ በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ አስፈላጊ ነው፡፡ ድርሰቶቼም ውስጥ ታሪክ ነው የምጽፈው፡፡ የገጸ ባሕርያት ወይም የግለሰቦች ታሪክ ሊሆን ይችላል፣ ግን ታሪክ ነው፡፡

ገዛኸኝ፡ አንድ ደራሲ ታሪክን በድርሰቶቹ ውስጥ እንዴት ሊጠቀም ይችላል? ታሪክን ዳግም መልሶ ከመበየን (redefine ከማድረግ) አንጻር ሚናው ምንድን ነው? ለምሳሌ አንተ ሥራዎችህ ውስጥ ጥሬው ታሪክ ከሚነግረን ውጪ ነው ልታሳየን የምትሞክረው?

አዳም፡ ለመዘርዘር እሄዳለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ታሪክ ሲባል ትላልቅ ተብለው የተሰየሙ ሰዎች ታሪክ አለ፡፡ እኔ በዛ በኩል አልመጣም፡፡ ስማቸው የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ባልገቡ ሰዎች ነው ታሪክ ለመናገር የምሞክረው እንጂ ታሪክን አልተውም (abandon አላደርግም)፡፡ ቦታው የት ነው? የተራ ሰዎች ሚና ምንድን ነው? እዚያ ውስጥ እንዴት ለውጧቸዋል? እንዴት ያን ይገነዘባሉ? በዚያ ዓይነት መልኩ ነው የማቀርበው፡፡

ገዛኸኝ፡ የአሁኑ ሥራህ መረቅ የአዲስ አበባን ታሪክ ከቁርቆራዋ ጀምሮ የሚዳስስ ነው፡፡ ለመሆኑ መረቅን ምንድን ነው መረቅ የሚያደርገው? ንጥረ ነገሩ (essence) ምንድን ነው በአጭሩ?

አዳም፡ የሆነ ምግብ ልበልህ… ወጥ ብትሠራ ብዙ ቅመሞች አሉ እዚያ ውስጥ የሚገቡ፡፡ እነዚያን ቅመሞች እንደ ሕዝብ፣ እንደ ሰው፣ እንደ ግለሰብ ውሰዳቸው፡፡ እንደ ገጸ ባሕርይ እና ቅመም ምናምን አለ… እና ተፈልቶ የሚወጣ በኑሮ፣ በግጭት፣ በመፋቀር፣ በመጣላት በመሳሰለ ነገር ውስጥ የሆነ ውጤት አለ፡፡ ያ ውጤት መረቁ ነው፡፡ አጨራረሱ ነው፡፡ ሌላኛው ምንድን ነው? በግለሰብ ደረጃ ደግሞ የምትኖረው ሕይወት አለ፡፡ ቀደመም ሲል ያነሳሁት እንደ ማኅበረሰብ (community) ነው፡፡ …በግለሰብ ሕይወት ደግሞ የሚያገጥም አለ፣ ፍቅረኛ፣ ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ጓደኛ፣ እነዚህ ሁሉ ተሰባስበው የሚፈጥሩት ነገር አለ፡፡ ያ መረቀ ነው፡፡ እንደ ሰብዓዊ ፍጡር፣ እንደ ግለሰብ ራሱ ሐሳቡ አለ፡፡ እና እነዚህ ሚዛኖች በተለያየ ደረጃ ይመጣሉ… እና የመረቅ ሐሳብ ማለት የእነዚህ ነገሮች ግንኙነት ንጥር ውጤት ነው፡፡

ገዛኸኝ፡ በጊዜ መለኪያ ብናስቀምጠው መረቅ የትኛውን ጊዜ ይሸፍናል?

አዳም፡ ማለት ከነአላዛር ልጅነት፣ ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስከ 1976/77 ድረስ…

ገዛኸኝ፡ ድኅረ-ዘመናዊነት (postmodernism) የሚባለው ሐሳብ በልብ ወለድ ውስጥ ምናልባት ከአንተ ሥራዎች በኋላ ይመስለኛል ወደ ኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የተቀላቀለው… እንዲህ ብለው የሚተነትኑ የሥነ ጽሑፍ ምሑራን አሉ፡፡ እስቲ ይሄን ሐሳብ ለአንባቢያን በሚገባ መንገድ አፍታታልን፡፡

አዳም፡ እንደ እውነቱ እኔ ስጽፍ ድኅረ-ዘመናዊ (postmodern) ልጽፍ ነው፣ እውናዊ (Realist) ልጽፍ ነው አልልም፡፡ የማደርገው ምንድን ነው የሕይወትን ሂደት ነው የምከተለው፤ የገጸ ባሕርይዎቼን አካሄድ ነው የምከተለው፡፡ ንድፈ ሐሳቡን እነ ፀደይ ቢያብራሩ ይሻላል ይመስለኛል፡፡

ገዛኸኝ፡ እንደ ጸሐፊ የመጻፍ እንጂ የመተንተን ግዴታ ባይኖርብህም ላንተ ስሜት የሚሰጥህ ዘግው ወይም የአጻጻፍ ፈለግ ይኖራልና ራስህን የትኛው ውስጥ ትመድበዋለህ?

አዳም፡ ዘውጌ በመጠኑ ከዚያ የወጣ ይመስለኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የመረብ አጻጻፍ (Network Fiction) የሚባል አለ፡፡ የመረብ አጻጻፍ ገና ንድፈ ሐሳብ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ደግሞ እንደዛ ልጻፍ ብዬ ተነስቼ አይደለም፡፡ ሕጽናዊነት በሚል ከግራጫ ቃጭሎች ቀስ በቀስ እያደገ፣ አንዳንድ ነገሮች ደግሞ እየጠየቅኩ ስሄድ ልሠራው የምሞክረው ነገር ነው፡፡ ለእኔም ራሱ በመጠኑ እንግዳ ነገር ነው፡፡ እና የእኔ ቦታ ነው ብልም ገና አልያዝኩትም፣ ግን ወደዚያ ነው ያለሁት…

ገዛኸኝ፡ የራስህን ዘዬ (style) ወይም የአጻጻፍ ይትባሃል እየፈጠርክ ነው ያለኸው ማለት እንችላለን?

አዳም፡ አዎ፣ ግን ንድፈ ሐሳብ አቀንቃኝ (theoretician) ስላልሆንኩ ልቤን ሞልቼ ልነግርህ አልችልም፤ ትዕቢትም ሊመስል ይችላል፡፡

ገዛኸኝ፡ ላንተ ቅርጽ (form) ነው ይዘት (content) ይበልጥ የሚያሳስብህ?

አዳም፡ ሁለቱ ለየብቻቸው አይኖሩም ለኔ፡፡ እና አንድ ሴንጢ የሚወጋህ ሹል ስለሆነ ነው፤ ያ ነው ሴንጢ የሚያደርገው፡፡ ሹልነቱ ቅርጹ ነው፤ ቅርጹ ይዘቱ ነው፡፡ ስለዚህ ቅርጽ/ይዘት የሚለው ነገር ቀደም ያሉ ንድፈ ሐሳቦች ውስጥ የነበረ ነገር ነው፡፡ ለእኔ ሁለቱም አንድ ላይ መሄድ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ነው የመረብ አጻጻፍ ይበልጥ  የሚስበኝ፡፡

ገዛኸኝ፡ በብዙ ሥራዎችህ ውስጥ እውነታን ወደ ልቦለድ፣ ልቦለድን ወደ እውነታ እያመጣህ ትጽፋለህ፡፡

አዳም፡ ከባድ፣ ከባድ ጥያቄ ነው የምታመጣው... ዓለም ላይ እንደዛ ነው፡፡ እኔ በሆነ መልክ ልቦለድ (fiction) ነኝ፣ በሆነ መልክ የተቀናበርኩ (constructed) ነኝ፡፡ ይሄ የነጠረ (pure) አዳም ምንድን ነው? ወይም ይሄ የነጠረ ገዛኸኝ ምንድን ነው?  እ... የሆነ ከፋይ (proportion) አውጥተህ በሆነ መልክ ባትናገረውም የሆነ ውሸት አለኝ እኔ፡፡ እያንዳንዱ ግለሰብ የዚያ ዓይነት ውሸት አለው፡፡ ኩሸት በለው ውሸት ይኖራል፡፡ እና ርዕሰ ጉዳዩን ልለውጠውና ብዙ የመጠቀ (radical) ነገር አልሠራሁም፤ ተፈጥሯቸውን ነው ያሳየሁት፡፡ ስለዚህ ይሄ እውን (real) የምንለው ነገር የሆነ ውሸት ይኖረዋል፤ ከጀባው ውሸት ነው የምንለው ነገር የሆነ እውነት (truth) ይኖረዋል፡፡ አለበለዚያ አይኖርም አይኖርም፡፡ እና ቦታ ባለዋውጣቸው አዲስ ነገርም አይደለም፡፡ ድርጊት ነው አዲስ የሚያስመስላቸው፡፡ ድኅረ-ዘመናዊም (postmodern) ይባል፣ ምንም ይባል እንደዚያ አድርጎ ከታሪክ አምጥቼ ልብወለድ ውስጥ አስገባቸዋለሁ፡፡ ታሪክ ሲጻፍ የተነገረን እውነት ሳይሆን እናገኘዋለን፣ የሆነ ውሸት እናገኛለን፡፡ እዚ ውስጥ ቅንብር (construct) ናቸው፣ ያን በመረዳት ነው፡፡

ገዛኸኝ፡ ታሪክን አንዳንዴ ትፈለቅጣለህ (deconstruct) ታደርጋለህ?

አዳም፡ አዎን፣ ያንን ለማውጣት ነው፡፡ እውነቱን እና ሐሰቱን ለማውጣት ነው፡፡

ገዛኸኝ፡ በልብ ወለድህ ውስጥ ከተጠቀምክባቸው እውነተኛ ሰዎች አንዱ ስብሐት ነው፡፡ ስብሐት ላንተ ምንድን ነው? ማነው? ስብሐት የዕድሜውን እኩሌታ ጽፎ ተቀባይነት በይፋ ሳያገኝ የኖረ ደራሲ ነበር፡፡ አንተ በአንጻሩ ተቀባይነትን ያገኘኸው ከጠዋቱ ነው፤ ይሄን እንዴት ታየዋለህ?

አዳም፡ ስብሐትን እንደ ገጸ ባሕርይ አድርጌ የወሰድኩበት ምክንያት ስብሐት የሚስቡ (interesting) ነገሮች አሉት፡፡ የተለየ ደራሲ ነው፡፡ የተለየ ደራሲ ነው የምልበት ምክንያት በአንድ በኩል ውብ የሆኑ የአዲስ አበባ ተረቶች አሉት፤ ሕልማዊ (fantasy) የሆኑ፡፡ በሌላ በኩል ተፈጥሯዊ (naturalist) ወይም እውናዊ (realist) የሆኑ ጽሑፎች አሉት፡፡ እና እኔን የሱ የግል ታሪክ አይደለም የሚስበኝ፤ እሱ የግል ሕይወቱ ነው፡፡ ግን እንደ ሰበ-ሕዝብ (public-man) ባንድ በኩል ሕልማዊ (fantasy) በሌላ በኩል እውናዊ (realist) ጽሑፍ የጻፈበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ነው ያንን ልብ ወለድ የጻፍኩት... እና የተቻለኝን ያህል ሞክሬአለሁ፡፡

ገዛኸኝ፡ አንተ አሁን ወጣቶች ሲበቀሉህ እንዴት ታየዋለህ? ድርሰት በቀላሉ ታዋቂ የሚያደርግ አይደለም በእኛ አገር፡፡

አዳም፡ ይሄን መመለስ አልችልም፤ መጠናት አለበት፡፡

ገዛኸኝ፡ የአንባቢዎችህን ሁኔታ ስታይ ምን ስሜት ይፈጥርብሃል?

አዳም፡ አዎ፣ በጣም መስጦኛል፤ ለምን የሚለውን ግን መመለስ አልችልም፡፡ ይህ አንባቢዎች ጥናትን ይጠይቃል፤ ወይም ኅብረተሰብ-ነክ (sociological) ጥናት ይጠይቃል፡፡ ምናልባት እስካሁን ለወጣቶች ለምን፣ እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልስ ሥነ-ጽሑፍ አልነበረም፡፡ ይህን ጥያቄ አንባቢዎቹ ቢጠየቁና ለምን ወደዳችሁት ቢባሉ ይበልጥ መልስ የሚገኝ ይመስለኛል፡፡

ገዛኸኝ፡ ከኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የበለጠ የሚያሳስብህና ብዙ ጊዜ ደጋግመህ የምታውጠነጥነው የትኛውን ክፍል ነው? ከድርሰት ሥራህ አንጻር ማለቴ ነው፡፡

አዳም፡ የጥንት ታሪክ ይስበኛል፡፡ ከስማቸው ጀምሮ እንግዳነት አላቸው፡፡

ገዛኸኝ፡ ስለ ቃላት ካነሳን ደግሞ የሞቱ ወይም እየተረሱ ያሉ ቃላትን ትጠቀማለህ ብዙ ቦታ... እና አንተ ድጋሚ ነፍስ ዘርተህባቸው ሕይወታቸው እንዲቀጥል አድርገሃል... እንደ ፈርጥ ሊታዩ ይችላሉ በሥራዎችህ ውስጥ ፡፡ ለመሆኑ ሥራዬ ብለህ እየፈለግህ የምታገኛቸው ናቸው ወይስ...

አዳም፡ አንዳንዴ የማጠናቸው ቃላት አሉ... ደስ የሚሉት ቃላት ካገኘሁ የተለመዱ ቃላት ይሆኑና ይጥሙኛል፡፡ አንዳንድ ነገር እንግዳ ማድረግ፣ ስትጽፍ ዐረፍተ ነገርህ ውስጥ እንግዳ ነገር ሲገባ አንባቢ ይነቃል፡፡ ከቃላት ጀምሮ እስከ ሐረግ እስከተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች ድረስ... ያንን እንግዳ ነገር ሳስገባ፡፡ ስልቹ (cliché) የሆኑ ቃላት ፈልገህ በሐረግ ውስጥ በሆነ መልክ ፈትገህ አውጥተሃቸው እንዲያበሩ ማድረግ ትችላለህ፤ ከሞቱበት ታስነሳቸዋለህ ማለት ው፡፡

ገዛኸኝ፡ ቃላትን ትፈጥራለህ (coin ታደርጋለህ) ማለት ነው?

አዳም፡ አዎ፤ ቃላትን ስትፈጥር አዝናኝ ይሆናሉ፡፡ እና ትርጉም ይሰጣሉ፡፡ ድርሰት ደግሞ ያለ ቃላት አይሆንም፡፡ ቃላት ለኔ አስፈላጊ ናቸው፡፡

ገዛኸኝ፡ የተረሱ ወይም የሞቱ ቃላትን መጠቀም ለንባብ እንቅፋት ይሆናል የሚሉ አሉ፡፡ አደፍርስን ስናስብ ለመነበቡ እንቅፋት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ ቀበልኛ መጠቀሙ ነው ይላሉ፡፡

አዳም፡ ቀበልኛ (dialect) ተጠቅሜ አላውቅም፡፡ ለሆኑ ገጸ ባሕርያት ካልሆነ በቀር በሰፋት (extensive) አይደለም፡፡ እጠቁምሃለሁ ግን ባለመገንዘብ አይደለም፡፡ አንደኛ ቀበልኛ አላውቅም፣ ሕይወቴን የኖርኩት አዲስ አበባ ውስጥ ነው፡፡ የአዲስ አበባ አማርኛ የተለየ ነገር ነው፣ ግን ገጸ ባሕርያት ሲመጡ ለፍንጭ እጠቀማለሁ፡፡

ገዛኸኝ፡ የአዲስ አበባ ባህል የሚባል ነገር ያለ ይመስልሃል?

አዳም፡ አለ... እንዴ! እያንዳንዱ በአካባቢው የራሱ መኖሪያ መንገዶች አሉት፡፡ ቋንቋ አለ፣ አካሄድ፣ አለባበስ፣ ሠላምታ አሰጣጥ፣ የመደባደብ ቄንጥ ይኖራል፡፡ ግን እነዚያ ገንነው ሌላውን ላይወሩ ይችላሉ፡፡

ገዛኸኝ፡ ወጣት ሆነህ በጣም ደስ የሚልህ ነገር ምን ነበር? መዝናኛህ?

አዳም፡ ሲኒማ፣ ጥሩ ከሆነ የማንም ይሁን፡፡ የሕንድ ፊልም ጥቂት አይቻለሁ፡፡ ብዙ ግን የምዕራብ ፊልም ነው የማየው፡፡

ገዛኸኝ፡ የተባባልናት ጊዜ እያለቀች ነውና ምናልባት ለወጣቶች… ወደ ድርሰት ለሚመጡ የምትለው ነገር ካለ…

አዳም፡ ምንም አልልም፡፡ ደራሲን ነግረኸው አትፈጥረውም፡፡ እንደዚህ አድርግ ምናምን ስላልከው አይሆንም፡፡ የሚወዱትን ነገር ቢያደርጉ ጥሩ ነው፡፡ ደግሞ ጋዜጠኛው ቃለ መጠይቅ ሊያደርግ ሲወስድህ ጉንዳን ካለበት ቦታ ባይወስድህ… (ሃ! ሃ! ሃ!)

ገዛኸኝ፡ እንዲያው በመጨረሻ ስለቤተሰብህ ብትነግረን፡፡

አዳም፡ ባለትዳር ነኝ፡፡ ሁለት ልጆች አሉኝ፡፡

ገዛኸኝ፡ ልጆችህ ከሥነ ጽሑፍ ገር ግንኙነት አላቸው?

**አዳም፡** የለም፤ ከሳይንስ ነው፤ ትውውቃቸው ከሳይንስ ጋር ነው… ጥሩ አንኳር (solid) ሳይንስ ጋር…

ገዛኸኝ፡ በጣም አመሰግናለሁ አዳም፡፡ በሌላ ጊዜ ስትመጣ ደግሞ እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡